የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፯
ዲስ አበባ ህዳር ፳፬ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 7
ADDIS ABABA 3rd December, 2012

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፪/፪ሺ፭ ዓ.ም

ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስፋፊያ ድጋፍ ምዕራፍ ሦስት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ......................... ...........ገጽ ፮ሺ፮፻፷፱

CONTENTS

Proclamation No. 772/2012

African Development Fund Loan Agreement for Promoting Basic Services Program (PBS III) Project Ratification Proclamation ....... ............ Page 6669

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፪/፪ሺ፭

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስፋፊያ ድጋፍ ምዕራፍ ሦስት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፩፻፷፮ ሚሊዮን ዩ.ኤ (አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) ብድር የሚያስገኘው ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ ኦገስት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፲፫ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## PROCLAMATION No. 772/2012.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in an amount of 166,000,000 U.A (One Hundred Sixty Six Million Units of Account) for financing Promoting Basic Services Program (PBS III) was signed in Addis Ababa on the 24th day of August 2012;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 22nd day of November 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

| | |
|---|---|
| ያንዱ ዋጋ<br>Unit Price | 2.30 |

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስፋፊያ ድጋፍ ምዕራፍ ሦስት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፪/፪ሺ፭” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ ኦገስት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2100150027194 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፷፮ ሚሊዮን ዩ.ኤ (አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬ አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፳፬ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the “African Development Fund Loan Agreement for Promoting Basic Services Program (PBS III) Project Ratification Proclamation No. 772/2012”.

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement No. 2100150027194 signed in Addis Ababa on the 24th day of August 2012 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 166,000,000 U.A (One Hundred Sixty Six Million Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of December, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ